# ፊሽካው ተነፍቷል፣ ግን ጨዋታ የለም

ግርማ ካሳ

Friday, 06 May 2016 03:52 AM

የኢሳት ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን የጻፈዉን አንድ ጽሁፍ ዘሃበሻ ላይ አነበብኩ። መሳይ መኮንን በቅርቡ የጻፋት ትሁን ወይንም ዘሃበሻ ከዚህ በፊት መሳይ የጻፈውን ለጥፎት ይሁን ብዙ ግልጽ አልሆነልኝም። ለማንኛው በዚህ ጽሁፍ ዙሪያ አንዳንድ አስተያየት መስጠት ወደድኩ።

“ የ 23 ዓመት ወጣት ናት:: የአርበኞች ግንቦት 7 ተዋጊ ወታደር ስትሆን በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ተሳትፋለች” ይለናል መሳይ፣ ሃና ስለተባለች ያኔ ከአንድ አመት በፊት በኤርትራ ተዋዉቋት ስለነበረች አንዲት ኢትዮያዊት ሲጽፍ። ያን መጻፉ ችግር የለዉም። ግን ከአንድ አመት በፊት አስመራ ሄዶ የነበረ ጊዜ የተዋወቃትን ሴት ታሪክ በመጻፍ ስለ ግንቦት ሰባት ነው አንዳንድ ነገሮችን ሊነግረን ነው የሞከረው።

እስቲ ለወንድም መሳይ መኮንን ከታላቅ አክብሮት ጋር አንዳንድ ጥያቄዎች እንዳቀርብለት ይፈቀድልኝ:

1. ይች ኢትዮጵያዊት አሁን ያለችበትን ሁኔታ ያውቃል ወይ ? እንደ ጋዜጠኛ አሁን ያለችበትን ሁኔታ አጣርቶ፣ ካስፈለገም ቃለ መጠይቅ አድርጎ ማቅረቡንስ እንዴት ያየዋል ?

2. ይች ሴት በተለያዩ ዉጊያዎች እንደተሳተፈች ሲገልጽ የትኞቹና መቼ የተደረጉ ዉጊያዎች እንደሆኑ ተጨማሪ መረጃ ቢሰጠን ጥሩ ነበር። እንደሚታወቀው ግንቦት ሰባት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ነው እንጂ አንድም ቦታ ዉጊያ ያደረገበት ሁኔታ እንደሌለ ነው የምናወቀው።

አንድ ጊዜ በወልቃይት ፣ ሕዝቡ ከማንነት ጥያቄ ጋር በተገናኘ ከሕወሃት ሚሊሻዮች ጋር ተኩስ ልዉዉጥ ያደረገበት ሁኔታ ነበር። በዚያን ጊዜ ጋዜጠኛ መሳይ መኮንንና ኢሳቶች በቁም እሥር ያለውን ዘመነ ካሴን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ፣ “ፊሽካ ተነፍቷል፤ ወያኔ አለቀለት” ሲሉን ነበር። ከጥቂት ወራት በፊት ደግሞ በመተማ አንዳንድ ግጭቶች ሲፈጠሩ፣ ከመተማ ጎንደር ያለው መንገድ ሕዝቡ ዘግቶት የነበረ ጊዜ፣ ግንቦት ሰባቶች ብቅ አሉና በመተማ ዉጊያ እያደረግን ነን አሉ። በጣም እኮ ነው የሚገርሙት። ላለፉት አምስት ወራት በኦሮሚያ እንቅስቃሴ ሲደረግ ፣ አይናቸዉን በጨው አጥበው፣ ሕዝቡ መካከል ነን ብለው ጭራሹኑ አረፉት። በጣም ብዙ ያወራሉ ፤ ግን በተግባር የታየ ነገር የለም።



ምንም ነገር በሌለበት፣ ግንቦት ሰባት በሚደረጉ ትግሎች ሁሉ NO SHOW በሆነበት ሁኔታ፣ ወንድም መሳይ ፣እንደ ጋዜጠኛ፣ እዉነቱን ህዝብ እንዲያውቅ፣ የግንቦት ሰባት አመራሮች ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ የለበትም ወይ ?

3. ጋዜጠኛ መሳይ ስለዚህ ሴት አድናቆቱን ገልጿል። እኔም ትልቅ አክብሮትና አድናቆት ነው ያለኝ። የመረጡትን መንገድ ብቃወምም፣ ይች ሴት ሆኑ ብዙዎች ወደ ኤርትራ ምድር የሄዱት አገራቸው ስለሚወዱ ነው። ለአገራቸው እና ለሕዝባቸው ደማቸዉን ለማፍሰስ ነው። እነዚህ ወገኖች ጀግኖች ናቸው። “….ሃናን በአካል ሳገኛት በጣም ቁጥብ ነበረች:: ብዙ አትናገርም:: ታሪኳን እንድታጫውተኝ ያደረኩት ጥረት አልተሳካም:: ሲበዛ ዝምተኛ ናት:: ጀግና አይናገርም” ሲል ስለርሷ የጻፈውም ትክክል ነው። “የጣይቱ ልጅም” ብሏታል። ልክ ነው የጣይቱ ልጅ ናት።

ግን እንደ ሃና ያሉ ጀግና ሰዎች ኤርትራ ተቆልፎባቸው እንዲቀመጡ መደረጉ ሁላችንንም በተለይም በስፍራው ሄደው እነዚህን

ወገኖች ለተመለከቱ ለነ መሳይ መኮንን ሊያሳስባቸው አይገባም ነበር ወይ ?

በኔ ግምት በርግጥም ኤርትራ እንደ ሃና ላሉ ጀግኖች ቤርሙዳ ነው የሆነችው። ግንቦት ሰባት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ሕዝቡ ሕይወቱን እየከፈለ በሚታገልበት ወቅት፣ ፊሽካው ተነፍቷል ተብሎ ጨዋታ ብሎ ነገር የለም። የተዘፈነላቸው፣ ጀጋናው፣ አርበኛው የተባሉት የድርጅቱ መሪ ምን እያደረጉ እንደሆነ የት እንዳሉ የሚታወቅ ነገር የለም።

እነዚህንና የመሳሰሉት ጥያቄዎች እየጠየቁ የሕዝብን አደራ የተቀበሉ ጋዜጠኞች ለሕዝብ እዉነታውን የማሳወቅ ሃላፊነት አለባቸው። "ህዝቡ ግንቦት ሰባቶች ከአሁን ለአሁን መቼ ነው የሚመጡት ?"ብሎ ሲጠብቅ፣ ለካ እነርሱ ሕዝቡን ነው የሚጠብቁት" እንዳሉት አንድ ጦማሪ፣ ግንቦት ሰባት ታግሎ ህዝብን ነጻ ለማውጣት ሳይሆን ፣ ሕዝብ አምጾ ወያኔዎች ማስተዳደር ካቃታቸው፣ ደርግ ክፍተት ሲያገኝ ስልጣን እንደጨበጠው፣ ግንቦት ሰባቶች እንደ PLAN B ቀዉስ ከተፈጠረ ሰተት ብለው፣ ግርግሩን በመጠቀም ስልጣን ለመያዝ መሰለኝ እየተዘጋጁ ያሉት።

በግሌ ለኢሳት ጋዜጠኞ አክብሮት አለኝ። ኢሳት ትልቅና በጣም አስፈላጊ ሜዲያ ነው። ኢሳት እንደሚባለው የሕዝብ አይን እና የሕዝብ ጆሮ ከሆነ በታማኝነት ህዝብን ያገልግል። ኢሣት እዉነቱን ለሕዝብ ያቅርብ።፡የግንቦት ሰባት ወይን የሻእቢያ ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ መሆን የለበትም። ኢሳት በሕዝብ ዘንድ ትልቅ ቦታ ያለው ተቋም እንደመሆኑ ተግባራቱም ትልቅነቱን የሚያሳይ ይሁን። የግንቦት ሰባት ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ከሆነ ኢሳት ከነ ኢብሲ ( ኢቲቪ) መደዳ መመደቡ አይቀሬ ነው የሚሆነው። አንዳንዶቹ እንደዉም ኢሳትን የዳያስፖራ ኢቲቪ ማለት የጀመሩም አሉ።

ይቅርታ ይደረግልኝና፣ ብዙ ሰዎች ይሄን በማለቴ በስሜት ልትከፉ ትችላላችሁ። ግን በኤርትራ በኩል የሚደረገው ትግል የቁጩ ነው የሚመስለኝ። ከአሁን ለአሁን እነ ዶር ብርሃኑ ተዋግተው ነጻ ያውጡናል ብለን ተስፋ የምናደረግ ካለን ደግሞ እርማችንን ብናወጣ ነው የሚሻለው ባይ ነኝ። ከወያኔ መቶ እጥፍ ጭራቅ በሆነ ቡድን (ሻእቢያ) ድጋፍ የሚመጣ እንጥፍጣፊ መልካም ነገር ይኖራል ብዬ አላስብም። ግንቦት ሰባት ምጥርከሾ የሚባሉ፣ ድርጅታዊ ነጻነት የሌላቸው በሻእቢያ መመሪያ የሚወጡ፣ የሚገቡ፣ የሚቀመጡና የሚነሱ ቡድኖች ናቸው፣ እንደ ባዶ ታኒካ ድምጽ ማሰማት እንጂ የትም አይደርሱም። ሻእቢያ ካልፈቀደላቸው በስተቀር የራሳቸው አንዳች ፍቃድ የላቸውም።

ኢትዮጵያዉያን ለዉጥ በአገራችን እንዲመጣ ከፈለግን ትኩረቱን ወደ እያንዳንዳችን ነው ማዞር ያለብን። ቁልፉ ያለው እያንዳንዳችን ጋር ነው። አንጋጠን ወደ ኤርትራ መመልከታችንን አቁመን፣ እኛ ዉስጥ ያለውን አቅምና ፖቴንሻል ማየት መጀመር አለብን። ትግሉ ያለው አገር ዉስጥ ነው። ደከመም፣ በረታም አገር ዉስጥ ያለው ትግልን ከማጠናከር ዉጭ ሌላ መፍትሄና አማራጭ የለም።

ይሄን በመጻፌ ስህተት ተጽፏል የሚሉ ካሉ፣ ለመስማት ለመገሰጽ ዝግጁ ነኝ። ግን መረጃ ይዘው መሆን አለበት። ሌላው ይቅር ግንቦት ሰባት የቁጩ አለመሆኑን የሚይሳይ፣ ግንቦት ሰባት ነጻ ያወጣው አንዲት ቀበሌ ካለ ይንገሩን። ግንቦት ሰባት የዘጋው አንድ መንገድ ካለ ይጠቁሙን። የምር መሳሳታችንንና ግመታችን ትክክል አለመሆኑን ሰዎች ካሳዩን ለመታረም እና ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ነን። ስንጽፍ እናውቃለን ብለን አይደለም። በወቅቱ ትክክል ብለን ያመነበትን እንጂ የምንጽፈው።

ሁሌ የተለመደ ፈሊጥ ደግሞ አለ። "መጠላለፍ አያስፈለግም… ወያኔ ላይ ለምን አትበረቱም ..?." የሚል። ይህ አይነቱ አባባል ጸረ-ዴሞክራስያዊ አባባል ነው። ተቃዋሚ ነን ባዮች እየዋሹና ለሕዝቡ ባዶ ተስፋ እየሰጡ ዝም ብሏቸው ማለት በሕዝብ ላይ በደል መፈጸም ነው።

ሌላው "እናንተ ምን አደረጋችሁና ነው ሌላውን የምትተቹት ?" የሚሉም አሉ። ይሄም ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አስተያየት ነው። ማንም ዜጋ የፈለገውን አስተያየት፣ በፈለገው ጊዜ የመስጠት መብቱን የሚጋፋ ነው።

መጠየቅ ያለበት ማንም ጻፈ ፣ በማንም ላይ ተጻፈ፣ "የተጻፈው ነገር ትክክል ነው ወይ ?" የሚለው ጥያቄ ነው። ትክክል ከሆነ ከተጻፈው ነገር ላይ ትምህርቶችን ወስዶ ማሻሻያ የሚኖርበት ሁኔታ መፍጠር ነው። ትክክል ካልሆነ ደግሞ ትክክል አለመሆኑ በማሳየት የጸሃፊዉን ሐሳብ በሐሳብ በሰለጠነ መልኩ መጣል ነው።